ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ

Wisdom at the source of the Blue Nile

# በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ
# የሳይንስ ኮሌጅ የ2006 በጀት ዓመት የሥራ ዕቅድ

ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሕዳር 2006 ዓ.ም

# ማውጫ


ማውጫ ....1

I. መግቢያ ....2

II. በ2006 በጀት ዓመት የትኩረት አቅጣጫዎች....4

1. ከአመለካከት አንጻር፣ ....4

2. ከክህሎት አንጻር፣ ....6

3. ከአደረጃጀት አንጻር....8

4. ከአሰራር አንጻር....9

5. ከኮርስ አስተዳደር አንጻር ....10

6. ከስርዓተ ትምህርት አንጻር ....11

7. ከምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት አንጻር....12

8. ከመልካም አስተዳደር አንጻር ....13

III. የክትትልና ግምገማ ስልቶች....13

IV. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች....14

V. የኮሌጁ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና ዕሴቶች ....14

1. ተልዕኮ ....14

2. ራዕይ....14

3. እሴቶች ....15

VI. የ2006 ዕቅድ ዝርዝር ተግባራት....16

# I. መግቢያ

የአሁኑ ሳይንስ ኮሌጅ መምህራንን በዲፕሎማና ቀጥሎም በዲግሪ ደረጃ እያሰለጠነ ሲያስመርቅ ከነበረውና በኋላም የትምህርት ፋኩልቲ ተብሎ ከተደራጀው ከድሮው ፔዳጎጅ አካዳሚ የተወለደ ኮሌጅ ነው። በዩኒቨርሲቲው በተካሄደው ሥራን መልሶ የማደራጀት ጥናት ወቅት የቀድሞው የትምህርት ፋኩልቲ ወደ ተለያዩ የሥራ ክፍሎች ሲከፋፈል በአገር አቀፍ ደረጃ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ የትምህርት ዘርፎች የተሰጠውን ትኩረት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተፈጥሮ ሳይንስ ከ2001 ጀምሮ በኮሌጅ ደረጃ እንዲደራጅ ተደርጓል።

ሳይንስ ኮሌጅ በአሁኑ ጊዜ 231 መምህራንና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች አሉት። ከእነዚህ ውስጥ 134 መምህራንና 25 የቴክኒክ ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች በሥራ ላይ ያሉ ናቸው። በስራ ላይ ካሉ መምህራን መካከል 38 (28%) የዶክትሬት ዲግሪ ፣ 87 (65%) የማስትሬት ዲግሪና፣ 9 (7%) የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ናቸው። ከቴክኒክ ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች መካከልም 22ቱ (88%) የመጀመሪያ ዲግሪና ሌሎች 3 (12%) ዲፕሎማ (10+4) ያላቸው ናቸው።

ቀሪዎቹ 72 የሚሆኑት ደግሞ በትምህርት ላይ ያሉ ሲሆን 4ቱ (6%) ለድህረ ዶክትሬት 56ቱ(78%) ለዶክትሬት ዲግሪ እና 12ቱ (17%) ደግሞ ለማስትሬት ዲግሪ የሚያበቃቸውን ትምህርት በመከታተል ላይ ይገኛሉ። አዲስ ዕድል አግኝተው የሚማሩትን ሳይጨምር በትምህርት ላይ ያሉት ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲመለሱ የዶክትሬት ዲግሪ ያላቸው መምህራን ብዛት ወደ 48% ያድጋል ተብሎ ይጠበቃል።

ይህ አሃዝ በስትራቴጂክ ዕቅዳችን የተቀመጠውን የዶክትሬት፣ የማስትሬትና የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ስብጥር ግብ ቀድመን ማሳካት የምንችል መሆኑን ከማሳየቱም በተጨማሪ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥና ዩኒቨርሲቲውን የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለማድረግ ያለንን ራዕይ ለማሳካት ከፍተኛ አቅም የሚፈጥርልን ይሆናል።

ከስልጠና መስኮች አንጻር ኮሌጁ በ7 የቅድመ ምረቃ (ባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ፣ ኢንዱስትሪያል ኬሚስትሪ፣ ኧርዝ ሳይንስ፣ ሒሳብ፣ ፊዚክስና ስታቲስቲክስ)፣ በ5 የሁለተኛ ዲግሪ (በባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ፣ ሒሳብ፣ ፊዚክስና ማቴሪያል ሳይንስ የተለያዩ ስፔሺያላዜሽኖች) እና በአንድ የሶስተኛ ዲግሪ (ዶክትሬት ዲግሪ በስፔስ ፊዚክስ መስክ) መርሐ ግብሮች በማሰልጠን ላይ ይገኛል።

ኮሌጁ የትምህርት ተደራሽነትን ከማረጋገጥ አኳያ በቅድመ ምረቃ በመደበኛ፣ በክረምት፣ በተከታታይና በርቀት ትምህርት ፕሮግራሞች 4590 ተማሪዎችን ተቀብሎ በማሰልጠን ላይ ይገኛል። ከዚህ አኳያ በቅድመ ምረቃ መደበኛ ፕሮግራም 1549 (ከእነዚህ ውስጥ 40% ሴት ተማሪዎች)፣ በክረምት 1672 (19% ሴት ተማሪዎች)፣ በተከታታይ ትምህርት 32

((ከእነዚህ ውስጥ 28% ሴት ተማሪዎች) እና በርቀት 1352 ((ከእነዚህ ውስጥ 17% ሴት ተማሪዎች) ተማሪዎችን በማስተማር ላይ ነው፡፡ በማስተርስ ዲግሪ ፕሮግራም ደግሞ በመደበኛ 80 ((ከእነዚህ ውስጥ 17.5% ሴት ተማሪዎች) እና በክረምት 704 ((ከእነዚህ ውስጥ 17.5% ሴት ተማሪዎች) በድምሩ 784 ተማሪዎችን እንዲሁም በPhD ደረጃ 6 ተማሪዎችን በማሰልጠን ላይ ነው፡፡ ኮሌጁ በቅድመና ድህረ ምረቃ በጠቅላላው **5380** ተማሪዎች አሉት፡፡

**የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች (ሕዳር 2006 ዓ.ም)**

| ፕሮግራም | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|
| መደበኛ | 927 | 622 | 1549 |
| ክረምት | 1351 | 321 | 1672 |
| የማታ | 23 | 9 | 32 |
| ርቀት | 1116 | 221 | 1352 |
| ድምር | 3417 | 1173 | 4590 |

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሀገራችን የነደፈችውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ እውን ለማድረግ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት፣ ሀገራዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ጥናቶችና ምርምሮች በማካሄድ፣ ችግር ፈች የሆነ የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ የማኅበረሰብ አገልግሎት በመስጠት፤ የሀገራችንን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ልማት ለማፋጠን የበኩሉን ጥረት እያደረገ የሚገኝ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፡፡ ከተቋሙ አካል አንዱ የሆነው የሳይንስ ኮሌጅ ከዩኒቨርሲቲው የተሰጠውን ተልዕኮ ለመፈፀምና ራዕዩን ለማሳካት ከዩኒቨርሲቲያችን የረጅም ጊዜ ዕቅድ ጋር የተጣጣመ ዕቅድ በማውጣት ወሳኝ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡ የትምህርት ተደራሽነትን፣ ጥራትና አግባብነትን ለማረጋገጥና ለአካባቢው ማህበረሰብ ፋይዳ ያለው የማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የአጭርና የረዥም ጊዜ ዕቅድ በማውጣት ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

ኮሌጁ በ2005 በጀት ዓመት በርካታ ተግባራትን አቅዶ ያከናወነና ለውጥ ያስመዘገበ ሲሆን በ2006 በጀት ዓመትም ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በመለየት ለማቀድ ተሞክሯል፡፡ በ2005 በጀት ዓመት ኮሌጁ ከእቅድ አኳያ የነበረው አፈጻጸም እንደ አጠቃላይ ሲታይ አበረታች ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም ካለው አቅም አንጻር አሁንም የበለጠ መስራት እንደሚቻል አመላካች ጉዳዮች አሉ፡፡ በያዝነው ዓመት የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ በተደራጀ አግባብ የበለጠ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ትኩረት የሚደረግባቸው ዋና ዋና

ነጥቦችም ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት ማረጋገጥ፣ አግባብነትና ጥራት ያለው ትምህርት በቅድመና ድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች መስጠት፡ ችግር ፈቺ ምርምር ማካሄድ፣ የማኅበረሰብ አገልግሎት መስጠት እንዲሁም ለአገራችን ዕድገት የሚጠቅሙ የምርምርና የማኅበረሰብ አገልግሎት የልቀት ማዕከላትና የምርምር ቡድኖችን ማቋቋምና ወደ ስራ ማስገባት ይሆናሉ፡፡

## II. በ2006 በጀት ዓመት የትኩረት አቅጣጫዎች

### 1. ከአመለካከት አንጻር፣

ከዚህ ዕቅድ አንፃር አመለካከት ስንል ቅንነት፣ ራስን መመልከት፣ ክፍተቶች በታዩና ይታያሉ በተባሉ ቁጥር እጅን አጣጥፎ ችግሩን ወደ ሌሎች አካላት ከመግፋት ይልቅ በእኔ አቅም ምን ልሰራ እችላለሁ? ለመጭው ትውልድስ ምን ትቼ እሄዳለሁ? ብሎ ራስን መጠየቅን፣ ይቻላል ብሎ ማመን፣ ትኩረትን፣ ሐቀኝነትንና ፅናትን ያቀፈ ሆኖ ከዩኒቨርሲቲያችን ተጨባጭ ሁኔታ ሥራን የኔ ነው ብሎ ዩኒቨርሲቲውን በባለቤትነት ስሜት ማገልገልንና ለዩኒቨርሲቲው ያለንን የባለቤትነት ስሜት የተሰጠንን ተግባር በቅንነትና በታታሪነት በመፈጸም በተግባር ማሳየትን ያቀፈ ነው፡፡ በአጠቃላይ ሥራን በእቅድ የመምራትንና ከእቅዱ አኳያ የተቀመጡ ግቦችና ዒላማዎች በተቀመጠላቸው የአፈጻጸም ደረጃ መሠረት እንዲሳኩ አስፈላጊውን ተግባር ማከናወንና ወቅታዊ ክትትልና ግምገማ ማድረግን ይመለከታል፡፡

ከአመለካከት አኳያ የዩኒቨርሲቲው አመራር፣ መምህራን፣ ሠራተኞችና ተማሪዎች በ2005 በጀት ዓመት የዩኒቨርሲቲውን ራዕይ ለማሳካትም ሆነ የዕለት ተዕለት ክንውኖችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማሳካት በተቻለ መጠን ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲውና የኮሌጁ ዋና ደንበኛና ባለድርሻ የሆኑት ተማሪዎች ለዩኒቨርሲቲው ራዕይና ተልዕኮ መሳካት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ይህን ወሳኝ የሆነ ሚናቸውን ገንቢ በሆነ ሁኔታ እንዲጫወቱ ካስፈለገ በዩኒቨርሲቲው የመማር ማስተማርና ሌሎች ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ በሚሰሩ ስራዎችና በውሳኔዎች ላይ ተሳታፊ ሊሆኑና ትክክለኛ የሆነ አመለካከት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በመሆኑም ኮሌጁ በ2005 በጀት ዓመት በወሳኝነት ካከናወናቸው ተግባራት መካከል ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ወቅት ሊይዙት ስለሚገባ ሥነምግባርና ስለመማር ማስተማር ሂደት ግንዛቤ መፍጠርና ተማሪዎችን በተደራጀ አግባብ በመደበኛነት ማወያየት ይገኝበታል፡፡ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ የመጡበት ዋና ዓላማ ተገቢውን ዕውቀትና ክህሎት በመጨበጥ በመልካም ስነምግባር የታነጹ አምራች ዜጎች ለመሆን መሆኑን እንዲገነዘቡ

ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ይህም በመሆኑ በ2005 ዓ.ም ከመቼውም ጊዜ በተሻለ ሁኔታ ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት ታይቷል፡፡ ተማሪዎች ጥያቄያቸውን በሰላማዊ ሁኔታ የማቅረብ መልካም ጅማሮ አለ፡፡ ይህን ይበልጥ ለማጠናከር በያዝነው ዓመትም ተከታታይ የማወያየትና ከሕግ ውጭ የመንቀሳቀስ ፍላጎት ያለቸው ካሉም የእርምት እርምጃ የመውሰድ ሥራ መሰራት ይኖርበታል፡፡

ባለፈው በጀት ዓመት ለነባርና አንደኛ ዓመት ተማሪዎች ስለሞጁላር የትምህርት አሰጣጥ፣ ተግባር ተኮር ትምህርትና ተከተታይ ምዘና እንዲሁም ስለ Peer-Led Learning የዩኒቨርሲቲውን Bylaw መሰረት በማድረግ ስልጠና በመስጠታችን በተማሪዎች ዘንድ የነበረውን ግራ መጋባት ለመቀነስ የተቻለ ሲሆን በዚህ ዓመትም በተለይ ለመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች ተመሳሳይ ስልጠና ለመስጠት ታቅዷል፡፡

ካለፈው ዓመት መልካም ተሞክሮ በመነሳት የትምሕርት ግብዐቶች አቅርቦት፣ የኮርስ አሸፋፈን፣ የተግባራዊ ትምህርት አሰጣጥ፣ የተከታታይ ምዘና፣ የምዘናዎች ግብረ መልስ አሰጣጥና የPeer-Led Learning አፈጻጸም ላይ ከየትምሕርት ፕሮግራሙ ካሉ የሴክሽን የተማሪ ተወካዮች ጋር መደበኛ ውይይት ይደረጋል፡፡ የመጽሐፍት ተማሪ ጥመርታን ቢያንስ አንድ መጽሐፍ ለአስር ተማሪዎች ከማድረስ አንጻር መጽሐፍትን ፎቶ ኮፒ በማድረግ አበረታች ውጤት የተገኘ ቢሆንም መጽሐፍትን መግዛት ግን የተሻለ አማራጭ በመሆኑ በ2006 ትኩረት የሚደረግበት ስራ ይሆናል፡፡

የጥናትና ምርምር ደረጃን ከማሳደግ አንፃር ተመራቂ ተማሪዎች ቀደም ሲል የተሰሩ የጥናት ወረቀቶችን በቀጥታ እንዳይገለብጡ ለመከላከል ለ2ኛ ዓመት የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ስለፕላጂያሪዝም የግማሽ ቀን ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ፕላጂያሪዝምን ለመከላከል ከግንዛቤ ፈጠራው ጎን ለጎን የተማሪዎችን የመመረቂያ ጽሁፎች ወደ ኮሌጁ ድረ ገጽ የመጫንና አግባብነት ያላቸውን የፕላጂያሪዝም መከላከያ ሶፍትዌሮች መጠቀም እንደ ዕቅድ ተይዞ ያልተከናወነ በመሆኑ በ2006 ዕቅዳችን ውስጥ ተካቶ መከናወን ይኖርበታል፡፡

በመምህራን በኩልም በ2005 ዓ.ም ቤተ ሙከራዎችን ለማደራጀትና ግብዓቶችን ለማሟላት የተደረጉ ጥረቶች፣ ሞጁላር የትምህርት አሰጣጥንና፣ ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ ለማድረግ የተደረጉ ጥረቶች፣ ኮሌጃችን አቅዶ ያስተናገደውን የመጀመሪያውን ዓመታዊ የሳይንስ ኮንፈረንስ በውጤታማነት ለማስተናገድ የተደረገው ርብርብና ለአንድ ውጤት በጋራ የመስራት መንፈስና የታየው ውጤት፣ በመምህራን በኩል ምርምሮችን ለመስራትና የማኅበሰብ አገልግሎት ለመስጠት የታዩ ተነሳሽነቶችና ጥረቶች፣ በኮሌጅና በትምህርት ክፍል ደረጃ ዓመታዊና ወርሀዊ እቅድ በማዘጋጀት ሥራን ለመፈጸም የተደረገው ጥረት በበጎ ጎን የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ ግብረ መልስ በመስጠትና Peer Led Learning ተግባራዊ በማድረግ በኩል አሁንም ያልተፈታ ችግር አለ። በቤተሙከራዎች የሚገኙና ለሚገዙ መሳሪያዎችና ኬሚካሎች ትክክለኛ ስፔሲፊኬሽን በማዘጋጀትና ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባ ግዥዎችን በመለየትና በመከታተል እንዲሁም ያሉንን ቤተ ሙከራዎች በባለቤትነት ስሜት በመጠቀምና በመጠበቅ ረገድ፣ ባለው አቅርቦትና በእኔ አቅም ምን ልሰራ እችላለሁ ከማለት ይልቅ ችግሮችን ሩን ወደ ሌሎች አካላት መግፋት ለመጭው ትውልድስ ምን ትቼ እሄዳለሁ? ብሎ ራስን መጠየቅ ላይ አሁንም ግልጽ የሆነ ችግር አለ። ተግባራትን ባልታቀደና በተለመደው አካሄድ ለመፈጸም የመፈለግ አዝማሚያ አሁንም ያልተሻገርነው ችግር ነው። ስለሆነም

*የባለቤትነት ስሜትን ለማጎልበት*

- *በዩኒቨርሲቲው ተልዕኮና ራዕይ ላይ መግባባት መድረስና የኮሌጁን ርዕይና ተልዕኮ በጋራ መወሰን፣*
- *በስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅዶች ዝግጅት ላይ መምህራንና ሰራተኞች ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማድረግ ያስፈልጋል።*
- *በየደረጃው ላሉ የሥራ ኃላፊዎችና መምህራን ተግባርና ኃላፊነታቸውን በግልጽ ማስቀመጥ፣*
- *ከመምህራን ጋር እንደአግባቡ በተናጠልም ቢሆን ውይይት ማድረግ፣*
- *አዲስ ለሚቀጠሩ መምህራንና ሰራተኞች የኢንዳክሽን ስልጠና መስጠት፣*
- *ግልጽ ውይይትና ግምገማ ማድረግ፣*
- *ወጥ የሆነ የአሰራር ማንዋል በማዘጋጀት መተግበር፣*
- *የስራ ዝርዝር በመስጠት የእያንዳንዱን ሠራተኛ አፈፃፀም በሚገባ ለመመዘን እንዲቻል የውጤት ተኮር አሠራርን ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ነው።*

## 2. ከክህሎት አንጻር፣

ክህሎት በዋናነት ሰዎች ስለሚሰሩት ሥራ ያላቸውን አቅምና ብቃት፣ ተግባሮቻቸውን በተጨባጭ የማቀድ፣ የማደራጀት፣ የመምራት፣ የመከታተልና የመገምገም፣ እንዲሁም ከግምገማው ከሚገኘው ግብረ-መልስ በመነሳት ተገቢውን የማሻሻያ ርምጃ የመውሰድንና በአጠቃላይ የሚያከናውኗቸው ተግባራት የዩኒቨርሲቲውን ተልዕኮና ራዕይ ከማሳካት አኳያ ያለውን ፋይዳ ጠንቅቆ የመረዳት ጉዳይን ይመለከታል። ዘመኑ የወለዳቸውን የአሠራር ስልቶች ተጠቅሞ ሥራን ውጤትና የተሻለ ለውጥ በሚያስገኝ ሁኔታ በማቀድና በመምራት በኩል እንዲሁም ለደንበኛ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት በሰለጠነ አኳኋን ማስናገድ ላይ

ጅማሮው ደህና ቢሆንም አሁንም ሰፊ ችግር እንዳለ ከ2005 በጀት ዓመት እቅድ አፈጻጸም ግምገማችን መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በዚህ የበጀት ዓመት በመምህራንና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ሊሰሩ ስለታሰቡ የክህሎት ማዳበሪያ ተግባራት በአጭሩ ቀርቧል፡፡

ሁሉም የኮሌጁ የአስተዳደር ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች በ2006 በጀት ዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትና እነሱ የተመደቡበት ኃላፊነት የሚያስፈልገውን ሙያ እንዲያካብቱ ያለመ ስልጠና ለመስጠት እቅድ ተይዟል፡፡ የስልጠናው ዋነኛ ትኩረት ፈጻሚዎች በሚሰሩበት የሙያ መስክ ክህሎታቸውን ለመጨመርና የደንበኛ አያያዝ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት ነው፡፡

በተለይ የቴክኒክ ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞችን በተመለከተ የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትና እነሱ የተመደቡበት ኃላፊነት የሚያስፈልገውን ሙያ እንዲያካብቱ ከሚሰራው ስራ በተጨማሪ ስለ ቤተሙከራ ክፍሎችና መሣሪያዎች አያያዝ፣ አሰራርና ደህንነት አጠባበቅ ስልጠና ይሰጣል፡፡

ባለፈው ዓመት የኮሌጃችን መምህራን ስለምርምር አሰራር የክህሎት ማዳበሪያ ስልጠና እንዲያገኙ በታቀደው መሰረት በአቅም ግንባታ ማዕከል አስተባባሪነት በኮሌጃችን የስታቲስቲክስ ትምህርት ፕሮግራም መምህራን ምርምር ለሚሰሩ የኮሌጃችንና የሌሎች ኮሌጆች መምህራን በመሰረታዊ የስታቲስቲካዊ መረጃ ትንተና ዘዴዎችና ለዚሁ ሥራ የሚረዱ ስታቲስቲካዊ ሶፍትዌሮች ላይ የክህሎት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ከሰልጣኝ መምህራን በተገኘው ግብረ መሰረት ስልጠናው ስለምርምር ተጨማሪ አቅም የሚፈጥር ነው፡፡ በመሆኑም በያዝነው ዓመትም ስልጠናውን ያላገኙ መምህራን እንዲሰለጥኑ የሚደረግ ይሆናል፡፡ የተማሪዎችን መጉላላት ለመቀነስ የዩኒቨርሲቲውን ሌጅስሌሽን መሰረት በማድረግ ተማሪዎችን ስለማማከርና ስለመርዳት እንዲሁም ስለተማሪ ማኅደር አያያዝ ከተማሪ አካዳሚክ አማካሪዎችና የደንበኞች ኬዝ ቲም ሰራተኞች ጋር ውይይት ይደረጋል፡፡

ከተማሪዎች ጋር በሚደረጉ ውይይቶች ለመረዳት እንደተቻለው አንዳንድ መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት ለተማሪዎች አመቺ በሆነ ሁኔታ ማቅረብ ላይ ክፍተቶች እንዳሉ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ አንዳንድ መምህራንም በዚህ ሃሳብ ይስማማሉ፡፡ በመሆኑም መምህራን ያወቁትን ለሌሎች የማሳወቅ ችሎታን ለማዳበር ያለመ ስልጠና ሊያገኙ ይገባል፡፡ ከዚህ አኳያ ስልጠናው የሚያስልጋቸው የኮሌጁ መምህራን የHDP ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ

ሌላው የመምህራንን ክህሎት ለማዳበር የሚሠራ ስራ የመምህራኑን የማስተማር አቅም መገንባት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የዚህ ስራ ትኩረት መምህራኑ የሚያስተምሩት የትምህርት

መስክ በየጊዜው የሚኖረውን የዕውቀት ዕድገት እየተከታተሉ ዕውቀት እንዲያገኙ ማስቻል ነው፡፡ ይህ የሚተገበረው ግልፅ የሆነ ፕሮግራም የወጣለት ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም በመተግበር ነው፡፡ ስለሆነም በሁሉም ፕሮግራሞች ክፍተቶችን በመለየት ተገቢ የሆነ የሙያ ማሻሻያ (Subject Matter Knowledge) ፕሮግራም መዘርጋት የዕቅዳችን አንዱ ትኩረት ነው፡፡ በዚህ ረገድ መምህራን አሁን ያለውን የኮርስ ቡድን አደረጃጀት በመጠቀም እርስ በርስ መማማር እንዲችሉ መደበኛ የውይይት ጊዜ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣

**በባዮሎጂ ትምህርት ፕሮግራም**

- በ GIS application /ለ10 መምህራን/
- በ Molecular techniques /ለ 5 መምህራን/
- በ Statistical package ስልጠና (SPSS, SAS) ለ10 መምህራን ስልጠና ይሰጣል

**በስታቲስቲክስ ትምህርት ፕሮግራም**

- በ Statistical package (Advanced SPSS, STATA, R እና SAS) ስልጠና ለ9 መምህራን ስልጠና ይሰጣል

**በፊዚክስ ትምህርት ፕሮግራም**

- በ Research Methodology ለ10 መምህራን
- C++, Latex, Matlab ለ7 መምህራን ስልጠና ይሰጣል

## 3. ከአደረጃጀት አንጻር

የሳይንስ ኮሌጅ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው ተቋማዊ ለውጥ የፈጠረውን አደረጃጀትና ሥራን በራስ የመምራት ውክልና በጠበቀ መልኩ የትምህርት ጥራትን ከማረጋገጥና መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አኳያ በርካታ ተግባራት አቅዶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

*ከአደረጃጀት አንጻር ኮሌጁ ካያዛቸው መሰረታዊ ዕቅዶች መካከል የተጀመረውን የኮሌጁን አደረጃጀት ማጠናቀቅና ወደ ስራ ማስገባት አንዱ ሲሆን ከዚሁ ጋር በተያያዘ የኮሌጁን ኮምፕሌክስ ለማሰራት የፕላን ዝግጅትና የቦታ መረጣ በዚህ ዓመት ለማጠናቀቅ ታቅዷል፡፡*

*ከዚህም በተጨማሪ የኢንዱስትሪያል ኬሚስትሪ ዘርፍን ከኬሚስትሪ በመለየት በተሻለ አደረጃጀት ራሱን የማስቻልና የማጠናከር ስራ ይሰራል፡፡ ከዚህ አኳያ ባለፈው ዓመት*

*የተጀመረው የኢንዱስትሪያል ኬሚስትሪ መሰረታዊ የስርዓተ ትምህርት ክለሳ በዚህ ዓመት ይጠናቀቃል፡፡*

የቤተ ሙከራዎችን አደረጃጀት በማጥናት እያንዳንዱ ቤተ ሙከራ ባለቤት ፐሮፌሰር እንዲኖረው ማድረግና ለቤተሙከራዎችም የአሰራር መመሪያ እንዲሁም ማንዋሎች ማዘጋጀት ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ *ባለፈው ያመት ታቅዶ ሳይከናወን የቀረው ቤተ ሙከራዎችን በካይዘን ማደራጀትም በዚህ ዓመት የመጀመሪያ አጋማሽ ይከናወናል፡፡*

ባለፈው የተጀመረውን ተማሪዎችን በአቻ ለአቻ ትምህርት (Peer Learning) እንደገና በማደራጀትና በመከታተል የተሻለ *ሥራ ለመሥራት* በአግባቡ አቅዶ *መንቀሳቀስን* ይጠይቃል፡፡ ከዚህ አኳያ በኮሌጁ የትምህርት ክፍልና የክፍል *ኃላፊ መምህራን* እንዲሁም የክፍል ተወካይ ተማሪዎች ስለአቻ ለአቻ ትምህርት ጽንሰ ሃሳብና የኒቨርሲቲው ስላዘጋጀው *መመሪያ* ስልጠና እንዲያገኙ ኮሌጁ የክትትልና የቁጥጥር ስራዎችን ተገቢ የሆነ ስርዓት ዘርግቶ ይሰራል፡፡

## 4. ከአሰራር አንጻር

ከአሰራር አንጻር የኮሌጁ ኮርስ ቼሮች የሚመሯቸውን ኮርሶች ከማስተዳደር አኳያ (ሞጁላር የትምህርት አሰጣጥ፣ ተግባር ተኮር ትምህርት አሰጣጥ፣ ተከተታይ ምዘናና ግብረ መልስን ተግባራዊ ማድረግ) በየሁለት ሳምንቱ ስለመማር ማስተማሩ ሪፖርት የሚያቀርቡበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከሪፖርቱ ይዘት ጀምሮ አቀራረቡም በዙ ወጣ ገባ የነበረበት *በዚህ ዓመት የተጠናከረ ክትትል የሚደረግበትን አሰራር እንዘረጋለን፡፡*

*ተማሪዎች ተግባራዊ ትምህርት እንዲያገኙ ለማድረግ የዓመቱ የኮሌጃችን አንዱ የትኩረት መስክ* ቤተሙከራዎችን ማጠናከርና ማደራጀት ሲሆን ከዚህ አኳያ ከግዥ ኤጀንሲ ጋር በመነጋገር ኬሚካልና አንዳንድ መሳሪያዎችን በውስን ጨረታ ለመግዛት የምንችልበት ሁኔታ እየተመቻቸ ነው፡፡

ካለፈው ዓመት መልካም ተሞክሮአችን በመነሳት የተማሪዎች ውጤትና አካዳሚክ መረጃዎች አውቶሜት የማድረግ ስራ አጠናክረን እንሰራለን፡፡ በ2006 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት በመደበኛ፣ በክረምት፣ በተከታታይና በርቀት ትምህርት ፕሮግራም የተመዘገቡ ሁሉንም የቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ ተማሪዎች መረጃ ሙሉ በሙሉ በSIMS የመመዝገብ *ሥራ* ይሰራል፡፡

እንዲሁም አስፈላጊ የተማሪዎን፣ መምህራንንና ሰራተኞችን መረጃዎችን በየጊዜው የማሻሻልና በኮሌጁ ዌብሳይት የመጫንና ዌብሳይቱን ወቅታዊ የማድረግ ስራም ይሰራል፡፡

በ2005 በጀት ዓመት በቤተ ሙከራ ስቶሮች ያሉ ኬሚካልና መሳሪያዎች በሚገባ ተለይተውና ተመዝግበው የተያዙ ሲሆን አሁንም እነዚህን መረጃዎች ወቅታዊ የማድረግ ተከታታይ ስራ ይሰራል፡፡

የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ባለፈው ዓመት ተጀምሮ ሳይጠናቀቅ የቀረውን የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ኮምፒቴንሲ ስኬል በማጠናቀቅ ተመራቂ ተማሪዎች ተመርቀው ከመውጣታቸው በፊት ተመርቀው ሲወጡ መያዝ የሚጠበቅባቸውን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት በተመለከተ አስቀድሞ በተዘጋጀ የማስተማሪያ ጽሁፍ እስከ ሁለት ሳምንት የሚደርስ ስልጠና እንዲያገኙና ይህን ተከትሎም የመውጫ ፈተና እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡ አሰራሩን እየጀመርነው እንደመሆኑ መጠን የመውጫ ፈተናውን ውጤት ተመስርቶ የሚወሰድ እርምጃ ባይኖርም ተመራቂዎች ያሉበትን ደረጃ እንዲያውቁ የሚያደርግ በመሆኑ ቀሪ ተማሪዎች የበለጠ እንዲሰሩ ያበታታል፡፡ በሂደት የመውጫ ፈተና ማለፍ የተሳናቸው ተመራቂዎች የትምህርት ማስረጃ የሚያዝበትን አሰራር መዘርጋት ለትምህርት ጥራት መረጋገጥ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የፈተናና የምዘና የአሰራር ስርዓት ይዘጋጃል፣

## 5. ከኮርስ አስተዳደር አንጻር

ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት የተለያዩ ግብዓቶችን የማሟላት (መምህራንን መቅጠር፣ በመማሪያ ክፍሎች የተሟላ ወንበር እንዲኖር ማድረግ፣ አረንጓዴና ነጭ ሰሌዳዎች መግዛት፣ መጻህፍት መግዛት፣ ለማስተማሪያ ቤተሙከራዎች ኬሚካልና አንዳንድ መሳሪያዎችን መግዛት) ስራ እንሰራለን፡፡

ሞጁላራይዜሽንን ሙሉ በሙሉ ከመተግበር በተጨማሪ በትምህርት አሰጣጥ ዕቅድ (ኮርስ ጋይ ቡክ) በመመራትና የተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴን በመጠቀም ኮርሶች ሙሉ በመሉ የሚሸፈኑበት፣ በተግባር የተደገፈ ትምህርት የሚሰጥበት፣ ተከታታይ ምዘና የሚደረግበትና የምዘና ግብረ መልስ በወቅቱ የሚሰጡበት እንዲሁም የተማሪ ውጤት በካሌንደር መሰረት የሚሰጥበት የክትትል አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች በቂ ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በተቻለ መጠን በተመረጡ ትምህርቶች ኢ-ለርኒንግ ተግባራዊ ለማድረግ ይሞከራል፡፡

ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት የመፃሀፍት ተማሪ ጥመርታን ለማሻሻል፣ የቤተ ሙከራዎችን አደረጃጀትና አሰራርና የቤተ መጽሀፍት አገልግሎቶችን ለማሻሻል በእቅድ ውስጥ ተካቷል፡፡ በዚህ ረገድ ባለፈው ዓመት የኮሌጁ የቤተ ሙከራዎች ዩኒት አባላት

የተለያዩ ተቋማትን የቤተሙከራ አደረጃጀትና አሰራር ልምድ እንዲቀስሙ የተደረገ ሲሆን የተገኘውን ልምድ ቀምሮ ለኮሌጁ ተስማሚ በሚሆን ሁኔታ አደረጃጀቱንና አሰራሩን የመንደፍና ተግባራዊ የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡

## 6. ከስርዓተ ትምህርት አንጻር

አሁን በአገር አቀፍ ደረጃ እየተካሄደ ያለውን የካሪኩለም ክለሳና የማስማማት (Harmonization) ስራ አጋጣሚ በመጠቀም በየትምህርት ፕሮግራሙ በአለም አቀፍ ደረጃ እየተሰጡ ያሉ አዳዲስ ኮርሶች ካሉ ለማካተት ይሞከራል፡፡ ባለፈው ዓመት የተጀመረው የኢንዱስትሪያል ኬሚስትሪ ፕሮግራም የካሪኩለም ክለሳ በዚህ ዓመት ይጠናቀቃል፡፡ ከተጀመረ ከሁለት ዓመት በላይ የሆነውና የባለቤትነት ጥያቄ በመነሳቱ ሂደቱ ተቋርጦ የቆየውን Environmental Sciences የቅድመ ምረቃ ካሪኩለም እልባት ለመስጠት ዕቅድ ተይዟል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን ዕውቅ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለማድረግ ከምንከተላቸው አንዱ መንገድ የድህረ ምረቃ ፕሮግራምን ማስፋፋት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ካለፈው ዓመት ጀምሮ ከዚህ በታች የተጠቀሱ የሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ አዳዲስ ፕሮግራሞችን ለመክፈት ስርዓተ ትምህርት በመጠናት ላይ ነው፡፡

- በሁለተኛ ዲግሪ (MSc) ፕሮግራም
  - ✓ በAquatic Resource Biology and Management
  - ✓ Applied Genetics
  - ✓ Conservation Biology
  - ✓ Environmental Sciences
  - ✓ Statistics
- በሶስተኛ ዲግሪ (PhD) ደረጃ
  - ✓ Applied Microbiology
  - ✓ Botanical Sciences
  - ✓ Algebra
  - ✓ Numerical Analysis
  - ✓ Real Analysis
  - ✓ Fluid Dynamics

በአሁኑ ሰዓት በድህረ ምረቃ ፕሮግራሞቻችን ያለውን የተማሪ ቅበላ መቀዛቀዝ ምክንያት በማጥናት አስቸኳይ መፍትሄ መስጠት ይገባል፡፡ በመሆኑም የሌሎችን ዩኒቨርሲቲዎች አሰራር ልምድ በመቅሰምና በመቀመር የተሻሻለ ስርዓት መዘርጋትና ፕሮግራሞቻችንም በዌብሳይታችንና በተለያዩ መንገዶች በመጠቀም የማስተዋወቅ ስራ ይሰራል፡፡ የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን የመመረቂያ ጽሁፍ ዝግጅት በተመለከተ የአሰራር መመሪያና ስታንዳርድ ይዘጋጃል፡፡

## 7. ከምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት አንጻር

ችግር ፈች ምርምር ከማካሄድና የማህበረሰብ አገልግሎት ከመስጠት አንፃር ልምድ ባላቸው መምህራን የሚመሩ የምርምር ቡድኖችን ማቋቋም እንደወሳኝ ስልት ተወስዷል፡፡ በዚህ ረገድ ባለፈው ዓመት 15 የምርምር ቡድኖች የተቋቋሙ ሲሆን ከእነዚህ ቡድኖች ውስጥ ብዙዎቹ በዚህ ዓመት የምርምር ንድፈ ሃሳቦች አቅርበው ወደ ምርምር ገብተዋል፡፡ በዚህ ዓመትም እነዚህን የምርምር ቡድኖች ማጠናከርና 5 የሚሆኑ ተጨማሪ የምርምር ቡድኖችን ለማቋቋም ታቅዷል፡፡ በሚቋቋሙ ቡድኖች አማካይነት የምርምር በጀት አመዳደብ እና አጠቃቀም ስርዓት ይዘረጋል፡፡ በኮሌጁ ቢያንስ 3 የምርምር ልህቀት ማዕከላት ለማቋቋም ጥረት ይደረጋል፡፡

በመምህራን የሚሠሩ ምርምር ውጤቶችን ለማሰራጨት ይረዳ ዘንድ ኮሌጁ ከምርምርና ማኀበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚደንት ጽ/ቤት የተረከበውን Ethiopian Journal of Science and Technology (EJST) ሕትመት አጠናክሮ ለማስቀጠል ዋና ኤዲተር (Editor-in-Chief) የተመደበ ሲሆን በየጥናት ዘርፉም የሚያገለግሉ እጩ ተባባሪ ኤዲተሮች (Associate Editors) ዝርዝር በዋና ኤዲተሩ አማካኝነት ቀርቧል፡፡ ዝርዝሩ በኮሌጁ የአካደሚክ ካውንስል ሲጸድቅ ምደባው የሚደረግ ይሆናል፡፡ በአሁኑ ሰዓትም እጩ ተባባሪ ኤዲተሮች አማካኝነት ለጆርናሉ አማካሪ ቦርድ የሚሆኑ አንጋፋ የየዘርፉ ምሁራንን ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር የማፈላለግና ፈቃደኝነት የመጠየቅ ስራ በመሰራት ላይ ይገኛል፡፡ በርካታዎቹ ፈቃደኝነታቸውን በጽሁፍ አረጋግጠዋል፡፡ የጆርናሉ አሰራርና አደረጃጀት ተሰርቶ ሲጠናቀቅም ለዩኒቨርሲቲው ሴኔት ቀርቦ ተቀባይነት (Reputability) እንዲኖረው ለማድረግ ታቅዷል፡፡

አስቀድመው በተለዩ የማህበረሰብ አገልግሎት የትኩረት አቅጣጫዎች (Thematic Areas) የማኀበረሰብ አገልግሎት እንሰጣለን፡፡ በዚህ ረገድ በዚህ ዓመት በትምህርት ክፍሎች ከፍተኛ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ በርካታ የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች ታቅደዋል፡፡

የዩኒቨርሲውን ርዕይና ተልዕኮ መሰረት በማድረግ የኮሌጁን ቀጣይ አምስት ዓመታት ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት የዚህ ዓመት ስራችን ይሆናል፡፡

### 8. ከመልካም አስተዳደር አንጻር

መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አኳያ የዩንቨርሲቲውን ውሳኔዎች ለመምህራን ለማሳወቅ ስርአት መዘርጋት፣ የመምህራንን የቢሮ፣ የኮምፒዩተር፣ የወንበርና ጠረጴዛ ችግር መፍታት፣ ከመምህራን፣ ተማሪዎችና ሰራተኞች ለሚነሱ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ግልጽና አፋጣኝ ውሳኔ መስጠትና በመምህራን መካከል ያለውን መልካም ግንኙነት ለማጠናከር አንድ የጋራ የሽርሽር ፕሮግራም (Social event) ማካሄድ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

## III. የክትትልና ግምገማ ስልቶች

ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል ተከታታይ የክትትልና ድጋፍ ስራ በመስራት ጥንካሬዎቻችች ይበልጥ አጠናክረን መሄድና ድክመቶቻችን በተከታታይ ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡ በዚህ አንጻር፣

- ✓ የኮሌጁ አመራር አባላት (ዲን፣ ም/ዲን፣ ድህረምረቃ ምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት አስተባባሪ፣ ፕሮግራም ማኔጀር፣ ቤተ ሙከራ ማኔጀርና የደንበኞች አገልግሎት አስተባባሪ) በየሳምንቱ ረቡዕ ጠዋት፣
- ✓ የኮሌጁ አካደሚክ ካውንስል በየሳምንቱ ረቡዕ ከሰዓት በኋላ እየገናኙ የኮሌጁን አሰራር ይገመግማሉ፣ በቀጣይ ሳምንት ስለሚሰሩ ስራዎች አቅጣጫ ያስቀምጣሉ፣
- ✓ ሁሉም የትምህርት ፕሮግራሞች በየሳምንቱ በፕሮግራም ደረጃ ስብሰባ በማድረግ በዕቅዱ መሰረት ያከናወኗቸውን ተግባራት፣ ያጋጠሟቸውን ችግሮችና የተሰጡ መፍትሄዎችን ይገመግማሉ፤ በቀጣይ ሁለት ሳምንታት በሚሰሯቸውን ስራዎች ላይም ተወያይተው ይወስናሉ፡፡
- ✓ ከየትምህርት ፕሮግራሙ የተማሪዎች ተወካዮች ጋር በየሶስት ሳምንቱ አንድ ጊዜ ስለ መማር ማስተማር ሂደት፣ ተከታታይ ምዘና፣ ግብረ መልስ አሰጣጥ፣ የአቻ ለአቻ ትምህርት (Peer Learning) አተገባበርና እና በአገልግሎቶች አሰጣጥ ላይ አጠቃላይ ውይይት ይደረጋል፡፡

# IV. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች

- ✓ በአጠቃላይ ከአመለካከት አንፃር ዘላቂ በሆነ መንገድ ሥራ ወዳድነትን፣ ታታሪነትን፣ ለተቋሙ ቅድሚያ መስጠትን፣ ተግባብቶ መስራትን ወ.ዘ.ተ በኃላፊዎቻችንና በሠራተኞቻችን መፍጠር ላይ ገና ውስንነቶች አሉ፡፡ አንዳንድ መምህራንና ሰራተኞች ግፊት ካልተደረገ በስተቀር የትምህርት ፕሮግራሙ ጉዳይ የእኔ ጉዳይ ነው ብሎ በተነሳሽነት መሥራት ላይ ጅምሩ ቢኖርም ብዙ ይቀራል፡፡
- ✓ በማቴሪያል አቅርቦት ረገድም ከፍተኛ የሆነ የመማሪያ ክፍል እና የመምህራን ቢሮ እጥረት ያለ በመሆኑ ትኩረት ይሻል፡፡
- ✓ አሁን በዋናው ግቢ ደረጃ ያለው የፋይናንስ አስተዳደር አሰራር የግቢው ሁሉም ኮሌጆችና ፋኩልቲዎች በጀት በአንድ ላይ ተቀላቅሎ ወጭ የሚደረግ በመሆኑና የበጀት አጠቃቀም ሽሚያ በመኖሩ ኮሌጃችን ተግባራቱን ባወጣው ዕቅድ መሰረት ለመስራት ተቸግሯል፣ አንዳንድ የወጭ መደቦች ላይ ስራው ሳይሰራ ገንዘብ አለቀ የሚባልበት ሁኔታ እየተፈጠረ በመሆኑ አስቸኳይ መፍትሄ ይሻል፡፡
- ✓ የግዥ፣ ጥገናና ትራንስፖርት አገልግሎቶች አሰጣጦች ላይ አሁንም ያልተፈታ ከፍተኛ ችግር አለ፡፡

# V. የኮሌጁ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና ዕሴቶች

## 1. ተልዕኮ

በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት አንዱ የሳይንስ ኮሌጅ ነው፡፡ ኮሌጁ የዩኒቨርሲቲው አንድ አካል እንደ መሆኑ አገሪቱ የምትፈልገውን በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል በብዛትና በጥራት በማፍራት፣ አገራዊ ጠቀሜታ ያላቸው ጥናትና ምርምሮች በማድረግና የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ለአገራዊ ብሎም ዓለማቀፋዊ ዕድገት ጉልህ አስተዋጾኦ የማድረግ ተልዕኮን አንግቦ ይንቀሳቀሳል፡፡

## 2. ራዕይ

የሳይንስ ኮሌጅ ዩኒቨርሲቲያችን ***"እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2017 ዓ.ም. በአፍሪካ ከሚገኙ አስር ግንባር ቀደም የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ መሆን"*** የሚለውን ራእዕ ለማሳካት ይሰራል፡፡ እንደ ኮሌጅም በ 2017 ዓ.ም. ድረስ በአፍሪካ ከሚገኙ አስር ግንባር ቀደም የሳይንስ ዘርፍ የምርምር ተቋሞች አንዱ የመሆን ራዕይ አለው፡፡

## 3. እሴቶች

ዩኒቨርሲቲያችን ያስቀመጣቸውን እሴቶች

- ✓ Quality
- ✓ Discourse,
- ✓ Innovation,
- ✓ Integrity,
- ✓ Democratic culture,
- ✓ Social responsibility

ለማዳበር ሳይንስ ኮሌጅ የድርሻውን ለመወጣት ቁርጠኛ ሆኖ ይሰራል፡፡

# VI. የ2006 ዕቅድ ዝርዝር ተግባራት

| ግቦች | መለኪያ | መነሻ | መድረሻ (ግብ ) | ሩብ አመት 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | ፈጻሚዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **እይታ 1. ደንበኛ** | | | | | | | | |
| **ግብ 1.1 የመምህራንን እርካታ በማረጋገጥ በኮሌጁ ውስጥ ያላቸውን ቆይታ ማስረዘም** | | | | | | | | |
| **ተግባር** 1. የመምህራን የቢሮ ችግር መፍታት፣ | መቶኛ | | 100 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ዲን |
| **ተግባር** 2. ግዥ በማናወን የመምህራንን የወንበር፣ የጠረጴዛና የኮምፒዩተር ፍላጎት ማሟላት | መቶኛ | | 100 | | | ✓ | | ዲን |
| **ተግባር** 3. ከመምህራን ለሚነሱ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ግልጽና አፋጣኝ (በ2 ቀናት ውስጥ) ውሳኔ በመስጠት እርካታን ማረጋገጥ | መቶኛ | | 95 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ዲን |
| **ተግባር** 4. በመምህራንና ሠራተኞች ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር ለከሌጁ መምህራንና ሰራተኞች የሽርሽርና የመዝናኛኛ ፕሮግራም እንዲኖር ማድረግ (Social event ማካሄድ) | ቁጥር | 0 | 1 | | | 1 | | ዲን |
| **ተግባር** 5 የአካዳሚክ ስታፍን የእድገት መመሪያና ደንቦች መሰረት በማድረግ መምህራንና ቴክኒካል አሲስታንቶች እድገት እንዲያገኙ ማድረግ | ቁጥር | | አሟልተው የቀረቡትን በሙሉ | ባሟሉበት ጊዜ | | | | ዲን |
| **ግብ 1.2 ተማሪዎችን መመዝገብ** | | | | | | | | |
| **ተግባር** 1 ቅድመ ዝግጅት በማድረግ አዲስ ተማሪዎችን ተቀብሎ የህይወት ታሪክ ፎርም ማስሞላት | መቶኛ | | 100 | 100 | | | | ደንበኞች አገልግሎት |
| **ተግባር** 2 አዲስ ገቢ ተማሪዎችን በየፕሮግራሙ ሴክሽን መመደብና መታወቂያ መስጠት | መቶኛ | | 100 | 100 | | | | ደንበኞች አገልግሎት |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ተግባር** 3 አዲስ ገቢና ነባር ተማሪዎችን መመዝገብ | መቶኛ | | 100 | 100 | | | | ደንበኞች አገልግሎት |
| **ተግባር** 4 የነባር ተማሪዎችን ዉጤት አጠናቅሮ ያለፉትን መመዝገብ | መቶኛ | | 100 | 100 | | | | ደንበኞች አገልግሎት |
| **ግብ 1.3 የተማሪዎችን ተሳትፎ ማሳደግ** | | | | | | | | |
| **ተግባር** 1. ከተማሪ ተወካዮች ጋር በየሶስት ሳምንቱ መደበኛ ውይይት በማድረግና በመማር ማስተማር ዙሪያ ያሉባቸውን ችግሮች በመለየት መፍትሄ መስጠት | የእርካታ መጠን | | 95 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ም/ዲን ፕሮግራም ማናጀር |
| **ተግባር** 2. የተማሪዎች ተወካዮች ተማሪ ተኮር በሆኑ ውሳኔዎች እንደሳተፉ ማድረግ | ድግግሞሽ | አካደሚክ ካውንስል በየሳምንቱና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ | | | | | | ዲን |
| **ተግባር** 3 ለተመራቂ ተማሪዎች የስራ ፈጠራ ስልጠና እንዲሰጥ ማድረግ | ቁጥር | 1 | 1 | | 1 | | 1 | ም/ዲን |
| **ተግባር** 4 ለመጀመሪያ ዓመት የሳይንስ ቅድመና ድህረ ምረቃ ተማሪዎች አጠቃላይ የላብራቶር ህግና ደንብ/ሴፍቲ/ ስልጠና መስጠት | ቁጥር | | 1 | | | 1 | | የቤተ ሙከራ ማኔጀር |
| **ተግባር** 5. ለአንደኛ አመት ተማሪዎች ኦሪየንቴሽን መስጠት | ቁጥር | | 1 | | 1 | | | ም/ዲን |
| **ግብ 1.4 የተማሪዎችን እርካታ ማረጋገጥ** | | | | | | | | |
| **ተግባር** 1. ከፍተኛ ዉጤትና ልዩ ፈጠራ ላስመዘገቡ ሴትና ወንድ ተማሪዎች እውቅና መስጠት | ድግግሞሽ | 0 | 1 | | | 1 | | ዲን |
| **ተግባር** 2. ለሚቀርቡ የትምህርት ማስረጃ ጥያቄዎች ተገቢና ወቅታዊ ምላሽ መስጠት | መቶኛ | | 100 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ዲን |
| **ተግባር** 3. በአካዳሚክ አድቫይዘር የማማከር ችግር (ስህተት) የሚነሱ ችግሮችና ቅሬታዎችን መቀነስ | ቅሬታዎች በዓመት | | < 5 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ፕሮግራም ማናጀር |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ተግባር 4.** ተማሪዎች ለሚያቀርቡአቸው ጥያቄዎች አፋጣኝ ሕጋዊ ምላሽ በመስጠት የተማሪዎችን እርካታ ማረጋገጥ | መቶኛ | | 95 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | መምህራንና ሁሉም የስራ ኃላፊዎች |
| **ተግባር 5** ለተማሪዎች መረጃና (ኦፊሻል፣ ID card፣…)፣የስም ለውጥና ሌሎች አገልግሎቶችን መስጠት | የተሰጠበት ጊዜ | | በተጠየቀ በሁለት ቀን | | | | | የደንበኞች አገልግሎት |
| **ተግባር 6.** የ2006 ተመራቂ ተማሪዎችን ፋይል (Active) የተሟላ መሆኑን በማረጋገጥ GCR አዘጋጅቶ በጊዜው ማስመረቅ | መቶኛ | | 100 | | | | 100 | የደንበኞች አገልግሎት |
| **ተግባር 7** ለተመራቂ ተማሪዎች መረጃ (Temporary Degree) በወቅቱ መስጠት | የቀናት ብዛት | | 3 | | | | ✓ | ዲንና የደንበኞች አገልግሎት |
| **ተግባር 8.** የ2003፣ 2004 እና 2005 ዓ.ም. ተመራቂ ተማሪዎችን መረጃ በማሟላት ለዋናው ሬጅስትራር ማስረከብ | መቶኛ | 0 | 100 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ደንበኞች አገልግሎት |
| **ተግባር 9** የመደበኛ ተማሪዎችን የወጭ መጋራት ፎርም ማስሞላት | መቶኛ | | 100 | | | | 100 | ደንበኞች አገልግሎት |
| **እይታ 2. የውስጥ አሰራር ሂደት** | | | | | | | | ዲን |
| **ግብ 2.1** የተደራጀ የተማሪዎች ሀርድ ኮፒ መረጃ መያዝ | መቶኛ | | 100 | | | ✓ | | የደንበኞች አገልግሎት |
| **ተግባር 1.** የቅድመና ድህረ-ምረቃ መደበኛ፣ተከታታይና የርቀት ተማሪዎች ዉጤት በካሌንደሩ መሰረት መግባቱን ማረጋገጥ | መቶኛ | | 100 | | ✓ | | ✓ | ፕሮግራም ማኔጀር |
| **ተግባር 2.** የሁሉም ተማሪዎች ዉጤት (Grade Report) በጊዜው ለአድቫይዘሮችና ለተማሪዎች እንዲደርስ ማድረግ | መቶኛ | | 100 | | ✓ | | ✓ | ደንበኞች አገልግሎት |
| **ግብ 2.2. የተማሪዎችን መረጃ አውቶሜት ማድረግ** | | | | | | | | |
| **ተግባር 1** የቅድመ ምረቃ መደበኛ፣ ክረምት፣ ተከታታይና የርቀት ትምህርት ስርዓተ ትምህርቶች፣ የተማሪዎችን የህይወት ታሪክና ውጤት ወደ SIMS ማስገባት | መቶኛ | | 100 | | 50 | 100 | | ደንበኞች አገልግሎት |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ተግባር 2** የድህረ ምረቃ መደበኛና ክረምት ትምህርት ስርዓተ ትምህርቶች፣ የተማሪዎችን የህይወት ታሪክና ውጤት ወደ SIMS ማስገባት | መቶኛ | | 100 | | 100 | | | ም/ዲንና፣ ደንበኞች አገልግሎት |
| **ግብ 2.3. የመምህራንንና ሰራተኞችን ፕሮፋይል የተመለከተ ሙሉ ዳታ ቤዝ መያዝ** | | | | | | | | ዲን |
| **ግብ 2.4. ቤተ ሙከራዎችን ማደራጀት** | | | | | | | | |
| **ተግባር 1** በቤተ ሙከራ ስቶሮች የሚገኙ ንብረቶችን ቆጠራ ማድረግና በኮምፒዩተር መዝግቦ መያዝ | መቶኛ | 50 | 90 | | ✓ | ✓ | ✓ | ቤተ ሙከራ ማናጀር |
| **ተግባር 2** ስለካይዘን አሰራር ለመምህራንና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ስልጠና መስጠት | የሰልጣኝ ቁጥር | 0 | 50 | | 50 | | | ዲንና የቤተ ሙከራ ማናጀር |
| **ተግባር 3** ቤተሙከራዎችን በካይዘን ማደራጀት | የተደራጁ ቤተሙከራዎች ቁጥር | 0 | 10 | | | 10 | | ቤተ ሙከራ ማናጀር |
| **ተግባር 4** የቤተሙከራዎች የስራ ማንዋል ማዘጋጀት | ቁጥር | | 29 | | ✓ | ✓ | ✓ | ት/ት ፕሮግራሞችና ቤተ ሙከራ ማናጀር |
| **ተግባር 5** በስታንዳርድ መሠረት የኮሌጁን ቤተ ሙራዎች ፓርቲሽን ማሰራት | ቁጥር | | | | | | | ቤተ ሙከራ ማናጀር |
| **ተግባር 6** መደበኛ በሆነ ሁኔታ የቤተ ሙከራ ማቴሪያሎች ጽዳት እና ቆጠራ ማካሄድ | ቁጥር | | | | 1 | | 1 | ቤተ ሙከራ ማናጀር |
| **ተግባር 7.** ግላስ ብሎዊንግ ዩኒት ማቋቋም | | | | | | ✓ | | ቤተ ሙከራ ማናጀር |
| **ተግባር 8.** ለቤተ ሙከራ ኢንስትረክተርና ረዳቶች ተከታታይ የግምገማና ክትትል ሥርዓት መዘርጋትና ክትትል ማድረግ | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ቤተ ሙከራ ማናጀር |
| **ተግባር 9.** የቤተ ሙከራ ባለቤት ፕሮፌሰሮች ምደባ ማድረግ | ቁጥር | 0 | 15 | | 15 | | | ዲን |
| **ተግባር 10.** የቤተ ሙከራዎችን አሰራር የተመለከተ የስራ መመሪያ (Guideline) ማዘጋጀት | | 0 | 1 | | | 1 | | ቤተ ሙከራ ማናጀር |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ተግባር** 11. በወጣው ስታንዳርድ መሰረት ለቤተ ሙራዎች ደረጃ መስጠት | | | | | | | | ቤተ ሙከራ ማናጀር |
| **ግብ 2.5. የኮሌጁን ዌብ ሳይት ወቅታዊነት መከታተል** | | | | | | | | |
| **ተግባር** 1 የኮሌጁ ዌብሳይት አሰርቶ ተግባራዊ ማድረግ | ቁጥር | 0 | 1 | 1 | | | | **ዲን** |
| **ተግባር** 2 መረጃዎችን በየጊዜው በኮሌጁ ዌብሳይት መጫንና ዌብሳይቱን ወቅታዊ ማድረግ | ወቅታዊነት በመቶኛ | | 90 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ዲንና ም/ዲን |
| **ግብ 2.6. የትምህርት ግብዓቶችን ማሟላት** | | | | | | | | ዲን |
| **ተግባር** 1. **የመምህራን ቅጥር መፈጸም**<br>✓ **ኬሚስትሪ** PhD 2, በMSC 3. ቴክኒካል ረዳት 6<br>✓ **ኧርዝ ሳይንስ** PhD 4, በMSC 4. ቴክኒካል ረዳት 1<br>✓ **ሂሳብ** 2 ፕሮፌሰሮች፣ 1 ቴክኒካል ረዳት<br>✓ **ስታቲስቲክስ** PhD 2, MSc 5 | | | | ✓ | | ✓ | | ኮስር ቼሮችና ም/ዲን |
| **ተግባር** 2. የመማሪያ ክፍሎችን ማስጠገን ቀለም ማስቀባት እና ማራኪ ማድረግ፡፡ | መቶኛ | | 100 | 100 | | | | ፕሮግራም ማናጀር |
| **ተግባር** 3. በመማሪያ ክፍሎች አረንጋዴ ሰሌዳ ማሟላት | ቁጥር | 0 | 20 | | ✓ | ✓ | | “ |
| **ተግባር** 4. በመማሪያ ክፍሎች ወንበር ማሟላትና ብክነትን ለመከላከል መቆለፍ | ቁጥር | | 300 | 200 | | 100 | | “ |
| **ተግባር** 5. በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የተሰባበሩ ወንበሮችን በማስጠገን አገልግሎት ላይ ማዋል | ቁጥር | | 150 | 50 | | 100 | | |
| **ተግባር** 6. መጽሃፍትን በግዥና በፎቶ ኮፒ በማባዛት በኮሌጁ ለሚሰጡ ሁሉም ኮርሶች 1 መጽሐፍ ለ 10 ተማሪ መድረሱን ማረጋገጥ | መቶኛ | 95 | 100 | | | 100 | | ም/ዲን |
| **ተግባር** 7. የማስተማሪያ ቤተ ሙከራዎች ኬሚካልና መሰረታዊ መሳሪያዎችን በመለየት እንዲሟሉ ማድረግ | መቶኛ | | 75 | | 50 | **75** | | ቤተ ሙከራ ማናጀር |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ተግባር 8.** ለሒሳብና የኽርዝ ሳይንስ ትምህርት ትምህርት ክፍሎች ኮምፒዩተር ላቦራቶሪ ማደራጀት | ቁጥር | | 2 | | | 1 | 1 | ዲንና የት/ክፍሉ |
| **ተግባር 9.** የኽርዝ ሳይንስ ትምህርት ክፍል ቤተሙከራና ስቶር ማቋቋምና ማደራጀት | መቶኛ | | 50 | | | 10 | 50 | የትምህርት ክፍሉ |
| **ተግባር 10.** የምርምርና ድህረ-ምረቃ ቤተ-ሙከራዎች የመሣሪያዎችና ኬሚካሎች ስፔስፊኬሽን ማዘጋጀት | | | | | | | | የሚመለከታቸው የት/ክፍሎች |
| **ተግባር 11.** የምርምርና ድህረ-ምረቃ ቤተ-ሙከራዎች የመሣሪያዎችና ኬሚካሎች ግዥ ማከናወን | | | | | | | | ቤተ ሙከራ ማናጀር |
| **ግብ 2.7. ጥራት ያለው ትምህርት መስጠት** | | | | | | | | |
| **ተግባር 1.** በተከለሰው የሞጁሎች አደረጃጀት መሰረት የተጓደሉ ኮርስ ቼሮችን መመደብና ወደስራ ማስገባት | | | 100 | | | 100 | 100 | ዲን |
| **ተግባር 2.** ጥራት ያለው ትምህርት መስጠት፣ | | | 90 | | | 90 | 90 | |
| ✓ የክትትል ስርዓት መዘርጋት | ቁጥር | | 1 | | 2 | | | ዲን |
| ✓ ኮርስ ጋይድ ቡክ ማዘጋጀት | መቶኛ | | 100 | ✓ | | ✓ | | የኮርስ ኃላፊዎች |
| ✓ ኮርሶችን ሙሉ በሙሉ መሸፈን፣ | መቶኛ | | 100 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | መምህራን |
| ✓ በካሪኩለሙ መሰረት በተግባር የተደገፈ ትምህርት መስጠት፣ | መቶኛ | | 90 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | መምህራን |
| ✓ በኮርስ ጋይድ ቡክ መሰረት ተከታታይ ምዘና መስጠት | መቶኛ | | 100 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | መምህራን |
| ✓ የምዘና ግብረ መልስ ቢበዛ በአንድ ሳምንት ውስጥ መስጠት | | | 100 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | መምህራን |
| ✓ የየኮርሱን ውጤቶች ከdeadline በፊት ለሬጅስትራር ማስገባት | መቶኛ | | 100 | | ✓ | | ✓ | መምህራን |
| **ተግባር 3.** በአቻ ለአቻ ትምህርት (Peer Learning) አደረጃጀትን መከለስ | በመቶኛ | | 100 | ✓ | | ✓ | | ፕሮግራም ማናጀር |
| **ተግባር 4.** የአቻ ለአቻ ትምህርት (Peer Learning) ጽንሰ ሃሳብና የአሰራር መመሪያዎችን በተመለከተ ለክፍል ኃላፊ መምህራንና ተማሪዎች ስልጠና መስጠት | የተሰጠ ስልጠና ብዛት | 1 | 1 | | ✓ | | | ፕሮግራም ማናጀርና ም/ዲን |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ተግባር 5.** በሐርሞናይዝድ ካሪኩለም /ካታሎግ/ የተቀመጡ የላብራቶሪ ሴሽን ቁጥሮች መሠረት የላብራቶሪና የመስክ የተግባር ትምህርቶችን ማከናወን | መቶኛ | 60 | 90 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ቤተ ሙከራ ማናጀርና ት/ት ክፍሎች |
| **ለተግባር 6.** ልዩ የአካደሚክ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች ድጋፍ መስጠት | መቶኛ | | 90 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ት/ት ፕሮግራሞች |
| **ለተግባር 7.** በተመረጡ ኮርሶችኢ-ለርኒግ ተግባራዊ ማድረግ | ቁጥር | 0 | 2 | | | 2 | | ም/ዲንና ፕ/ማናጀር |
| **ግብ 2.8. ካሪኩለም ማሻሻልና የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞችን ማስፋፋት** | | | | | | | | |
| **ተግባር 1** አሁን ያሉትን ሁሉን የቅድመ ምረቃ ስርአተ ትምህርቶችን መከለስና ትምህርት ሚኒስቴር ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ሀርሞናይዜሽን ሰርቶና አጠናቆ ማቅጸደቅ | ቁጥር | | 6 | | 6 | | | ዲንና ፕሮግራም ማናጀር |
| **ተግባር 2.** ባለፈው ዓመት የተጀመረውን የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ኮምፒቴንሲ ስኬል ማጠናቀቅ | ቁጥር | 0 | 7 | | | 7 | | ት/ት ክፍሎች |
| **ተግባር 3.** በተዘጋጁ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ኮምፒቴንሲ ስኬል መሰረት ለተመራቂ ተማሪዎች ማሰልጠኛ ጽሁፍ ማዘጋጀት | ቁጥር | 0 | 7 | | | 7 | | ት/ት ክፍሎች |
| **ተግባር 4.** በተዘጋጁ የቅድመና ድህረ ምረቃ ተማሪዎች ኮምፒቴንሲ ማሰልጠኛ ጽሁፎች መሰረት ለተመራቂ ተማሪዎች አጠቃላይ ክለሳ ማድረግና የመውጫ ፈተና መፈተን | ቁጥር | 0 | 7 | | | | 7 | ት/ት ክፍሎች |
| **ተግባር 5 .** የድህረ ምረቃ ቅበላን ለማሳደግ ጥናት በማድረግ የማሻሻያ ሃሳብ ማቅረብ | ቁጥር | 0 | 1 | | ✓ | ✓ | | የድ/ም/ም/ማ/አ/ አስተባባሪ |
| **ተግባር 6.** በ2005 የተጀመረውን የኢንዱስትሪያል ኬሚስትሪ ፕሮግራም ካሪኩለም ክለሳ ማጠናቀቅ | | | | | | ✓ | | የትምህርት ፕሮግራሙ |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ተግባር** 4 አዳዲስ የቅድመና ድህረ ምረቃ ስርአተ ትምህርቶች ቀርፆ ማጸደቅ | | | | | | | | የድ/ም/ም/ማ/አ/ አስተባባሪና ፕ/ማናጀር |
| በመጀመሪያ ዲግሪ (BSc) ፕሮግራም<br>✓ Environmental Sciences | | | | | | ✓ | | ዶ/ር አሊ |
| በሁለተኛ ዲግሪ (MSc) ፕሮግራም<br>✓ በAquatic Resource Biology and Management<br>✓ Applied Genetics<br>✓ Conservation Biology<br>✓ Environmental Sciences<br>✓ Statistics | | | | | | ✓ | | ዶ/ር አያሌው<br>ዶ/ር ብዙአየሁ<br><br>ዶ/ር አሊ<br>ዶ/ር እሰይ |
| በሶስተኛ ዲግሪ (PhD) ደረጃ<br>▪ ሂሳብ<br>✓ Algebra<br>✓ Numerical Analysis<br>✓ Functional Analysis | | | | | | ✓ | | ዶ/ር ታደሰና<br>ዶ/ር ተስፋሁን |
| በሶስተኛ ዲግሪ (PhD) ደረጃ<br>▪ ባዮሎጂ<br>✓ Applied Microbiology<br>✓ Botanical Sciences<br>▪ ፊዚክስ<br>✓ Condensed Matter Physics | | | | | | | ✓ | ዶ/ር ሙሉጌታ<br>ዶ/ር ብርሃኑ<br><br>ዶ/ር ገ/እግዚአብሄር |
| **ግብ 2.9. ችግር ፈች ምርምሮች ማካሄድ** | | | | | | | | |
| **ተግባር 1.** ልምድ ባላቸው መምህራን የሚመሩ ተጨማሪ የምርምር ቡድኖችን ማቋቋም | ቁጥር | 15 | 5 | | 5 | | | የድ/ም/ም/ማ/አ/ አስተባባሪ |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ተግባር 2.** ቦታኒካል ጋርደን በማቋቋም በስሩ ግላስ ሀውስ፣ አኒማል ሀውስ፣ ቲሹ ካልቸር፣ የነርሰሪ ሳይትና ሀርባሬም የያዘ እንዲሆን የቅድመ ዝግጅት ተግባር ማከናወን | ቁጥር | | | | | ✓ | ✓ | ባዮሎጂ ት/ት ክፍል |
| **ተግባር 3.** በ2006 ለሚደረጉ ምርምሮች ፕሮፖዛል ማዘጋጀት | ቁጥር | | 40 | ✓ | | | | መምህራን |
| **ተግባር 4.** የምርምር ፕሮፖዛል ማጽደቅና በጀት መመደብ | ቁጥር | | 10 | | ✓ | | | ዲን |
| **ተግባር 5. በ2006 እና ከዚያ በፊት የተጀመሩ** ምርምሮችን ማካሄድ | ቁጥር | | 25 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | መምህራን |
| **ተግባር 6.** የምርምር ውጤቶችን በምርምር ሳምንትና በኮንፈረንስ ላይ ማቅረብ | ቁጥር | | 15 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | መምህራን |
| **ተግባር 7.** የምርምር ውጤቶችን በታወቁ ጆርናሎች ማሳተም | | | 5 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | መምህራን |
| **ተግባር 8.** የምርምር ቤተሙራዎችን ማቋቋም | ቁጥር | 1 | 3 | | | 2 | 1 | የት/ክፍሎችና የቤተ ሙከራ ማኔጀር |
| **ተግባር 9.** የጥናትና ምርምር ግኝቶችን፣ የመመረቂያ ጥናቶችንና ጽሑፎችን በት/ት ፕሮግራም ሴሚናር ማቅረብ | አማካይ ድግግሞሽ | | በየሁለት ሳምንት | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ት/ት ፕሮግራሞች |
| **ተግባር 10** የምርምር ልህቀት ማዕከላት ለማቋቋም ጥናት ማድረግና ማቋቋም | ቁጥር | 1 | 3 | | | 1 | 2 | ባዮሎጂ ት/ት ፕሮግራም |
| **ተግባር 12.** የድህረ ምረቃ ቴሲስ አዘገጃጀት፣ የማማከር፣ የፈተናና ውጤት አሰጣጥ መመሪያ ማዘጋጀት | ቁጥር | 0 | 1 | | | 1 | | የድ/ም/ም/ማ/አ/ አስተባባሪ |
| **ተግባር 11.** የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ቴሲስ በሲዲ መግባቱን ማረጋገጥና ወደ ኮሌጁ website እንዲገባ ማድረግ፡፡ | | | | | ✓ | ✓ | ✓ | የድ/ም/ም/ማ/አ/ አስተባባሪ |
| **ተግባር 12.** ከምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ም/ፕ/ጽ/ቤት የተረከበውን Ethiopian Journal of Science and Technology (EJST) ሕትመት አጠናክሮ ማስቀጠል | ቁጥር | 0 | 1 | | | 1 | 1 | ዲንና የድ/ም/ም/ማ/አ/ አስተባባሪ |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ✓ Editor-in- Chief መሾም | ቁጥር | 0 | 1 | | 1 | | | ዲን |
| ✓ የጆርናሉን አደረጃጀትና አሰራር አጥንቶ ማስፈቀድ | ቁጥር | 0 | 1 | | ✓ | ✓ | | Chief Editor |
| ✓ ጆርናሉ በዩኒቨርሲቲው ዕውቅና እንዲኖረው ማድረግ | | | | | | ✓ | | ዲንና Chief Editor |
| ✓ የምርምር ሥራዎችን እየቀበሉና እየገመገሙ ማሳተም | | | | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | የድ/ም/ም/ማ/አ/ አስተባባሪና Chief Editor |
| **ተግባር 13** የመጀመሪያውን የሳይንስ አገር አቀፍ ኮንፈረንስ በተመለከተ ሪፖርቱን ማደራጀትና Proceeding ማሳተም | ቁጥር | 0 | 1 | | | 1 | | ዲንና የድ/ም/ም/ማ/አ/ አስተባባሪ |
| **ተግባር 15** ሁለተኛውን የሳይንስ አገር አቀፍ ኮንፈረንስ ማካሄድ | ቁጥር | 0 | 1 | | | 1 | 1 | ዲን |
| ✓ የኮንፈረንስ አዘጋጅ ዐቢይና ንዑስ ኮሚቴዎችን መምረጥ | መቶኛ | | | | 100 | | | " |
| ✓ ኮንፈረንሱን ማካሄድ | | | | | | 100 | | የድ/ም/ም/ማ/አ/ አስተባባሪ |
| ✓ ኮንፈረንሱን መገምገምና ማጠቃለያ ሪፖርት ማዘጋጀት | | | | | | | 100 | " |
| ✓ Proceeding ማሳተም | | | | | | | 100 | " |
| **ግብ 2.10. የአካባቢውን ህብረተሰብ ችግር ሊፈታ የሚችል የማህበረሰብ አገልገሎት መስጠት** | | | | | | | | |
| **ተግባር 1** አስቀድመው በተለዩ የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች (Thematic Areas) የማኅበረሰብ አገልግሎት መስጠት | ቁጥር | | 30 | | | 10 | 20 | ዲን |
| ✓ በዩኒቨርሲቲያችን ካምፓሶችና በአንዳንድ ት/ቤቶች ግቢዎች የሚገኙ ተክሎችን ሳይንሳዊ ስም ፅፎ መለጠፍ<br>✓ ለት/ቤት መምህራን ስለ ቤተ ሙከራ ት/ት አሰጣጥ ማሰልጠን<br>✓ በአንዳንድ ት/ቤቶች ስለአመጋገብና ንጽህና አጠባበቅ ስልጠና መስጠት<br>✓ በአንዳንድ ት/ቤቶች ለመምህራን Subject matter ስልጠና | | | | | | ✓ | ✓ | የባዮሎጂ ት/ት ክፍል |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መስጠት | | | | | | | | |
| ✓ ከመሬት መንሸራተት፣ ከህንፃ መደርመስና መስመጥ ጋር የተያያዙ<br>✓ የኮንስትራክሽን ማትራጀያል መምረጥ፣ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ<br>✓ ከከርስ ምድር የንፁህ የመጠጥ ውሃ የተያያዙ ችግሮችን በተመለከተ አገልግሎት መስጠት<br>✓ ለሀገር ውስጥ ለውጭ ሀገር የማዕድን፣ የሲሚንቶ፣የነዳጅ ባለሃብቶች የማማከር አገልግሎት መስጠት<br>✓ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተግባበር የጅኦሎጅካልና ተያያዥነት ያላቸው ለህብረተሰብ ጥቅም የሚውሉ ጥናቶች ማድረግ | | | | | | ✓ | ✓ | የአርዝ ሳይንስ ት/ት ክፍል |
| ✓ Statistical Consultancy and data analysis center በማቋቋም መምህራንና ሌሎች የመንግሥት መ/ቤት ባለሙያዎች መሰረታዊ የስታቲስቲካዊ መረጃ ትንተና ዘዴዎችና የStatistical package ስልጠና እንዲያገኙ ማድለግ፣<br>✓ ለክልል መ/ቤቶች ባለሙያዎች ስለ ስታቲስቲካዊ መረጃና የመረጃ ትንተና ዘዴዎችና የስታቲስቲካዊ ሶፍትዎር አጭር (የ40 ሰዓት) ስልጠና መስጠት | | | | | | ✓ | ✓ | ስታቲስቲክስ ት/ት ክፍል |
| ✓ በቅርብ ት/ቤቶች ላሉ የኬሚስትሪ መምህራን ስልጠና መስጠት<br>✓ በአቅራቢ ት/ቤቶች ላሉ ተማሪዎች ሌክቸር መስጠት<br>✓ በአቅራቢያ ያሌ ት/ቤቶችን ቤተሙከራ ማደራጀትና ስለአሰራሩ ስልጠና መስጠት<br>✓ በገበያ ላይ ያሉ የኬሚስትሪ መጽሐፍቶችን ክሪቲካል ሪቪው በማድረግ ማሻሻያዎችን ማቅረብ<br>✓ ቆሻሻ አወጋገድን በተመለከ ስልጠና መሰጠት | የት/ቤቶች ቁጥር | 1<br>2<br>2<br>10<br>1 | | | | ✓ | ✓ | ኬሚስትሪ ት/ት ክፍል |
| ✓ ለ2ኛ ደረጃ ት/ቤት የሂሳብ መምህራን Elementary የሆኑ | | | | | | ✓ | ✓ | ሒሳብ ት/ት |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የስታትስቲክስ ትምህርት መስጠት<br>✓ በተሌዮ ዘርፎችለማህበረሠቡ የማማከር ስራ መስጠት<br>✓ የሶፍትዎርና መረጃ ትንተና ስልጠና ለማህበረሠቡ መስጠት | | | | | | | | ክፍል |
| **ተግባር** 2. የአካባቢ መልሶ ማገገም ተግባር ማከናወን (ችግኝ ተከላ፣ ቬቲ ቨር ሳር ተከላ፣ አረም ማስወገድ፣ Water Hyacinth, ) | | | | | | | ✓ | ዲን |
| **ተግባር** 3. የተማሪ ክበባት ማቋቋም፣ | | | | | | | ✓ | ዲን |
| **ተግባር** 4. በቆጠራ የተለዩና በስጦታ ወይም መወገድ ያለባቸዉ መሣሪያዎችና ኬሚካሎች መለየት | | | | | | ✓ | ✓ | ት/ት ክፍሎች |
| **ተግባር** 5. በቆጠራ የተለዩና በስጦታ ወይም መወገድ ያለባቸዉ መሣሪያዎችና ኬሚካሎች መስጠት/ማሰወገድ | | | | | | ✓ | ✓ | ቤተ ሙከራ ማኔጀር |
| **እይታ 3. ተቋማዊ አቅምን ማሳደግ** | | | | | | | | **ዲን** |
| **ግብ 3.1. የመምህራንን አቅም ማሳደግ** | | | | | | | | **ዲን** |
| **ተግባር** 1. የስልጠና ፍላጎት ጥናት ማድረግ፣ | | | | | | | | ም/ዲን |
| **ተግባር** 2. መምህራንን በማስተርስና ዶክትሬት ዲግሪ ማሰልጠን | ቁጥር | | | | | | | |
| **ተግባር** 3. መምህራን ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋር የተገናኘ ስልጠና (Subject Matter Knowledge) እንዲያገኙ ማድረግ<br>**በባዮሎጂ ትምህርት ፕሮግራም**<br>▪ በ GIS application /ለ10 መምህራን/<br>▪ በ Molecular techniques /ለ 5 መምህራን/<br>▪ በ Statistical package ስልጠና (SPSS, SAS) ለ10 መምህራን ስልጠና ይሰጣል<br>**በስታቲስቲክስ ትምህርት ፕሮግራም** | ቁጥር | 0 | 34 | | | 10 | 24 | ዲን |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ▪ በ Statistical package (Advanced SPSS, STATA, R እና SAS) ስልጠና ለ9 መምህራን ስልጠና ይሰጣል | | | | | | | | |
| **ተግባር 4.** መምህራን የምርምርና መረጃ ትንተና ዘዴዎች መሠረታዊ ክህሎትና እውቀት እንዲያገኙ ስልጠና መሰጠት | የመምህራን ቁጥር | | 50 | | | **50** | | ዲን |
| **ተግባር 5.** መምህራን የማስተማር ክህሎት HDP ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ | | | 7 | | | 10 | 20 | ዲን |
| **ተግባር 6.** መምህራን ወደ ተለያዩ ተቋማት ሄደው የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ማድረግ | | | 20 | | | 20 | | ዲን |
| **ተግባር 7.** ለኮሌጁ የአስተዳደር ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች (ጸሃፊዎች፣ የደንበኞች አገልግሎት ሰራተኞች፣ የቤተ መጻህፍት ሰራተኞች) የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትና የተመደቡበት ኃላፊነት የሚያስፈልገውን ሙያ እንዲያካብቱ ያለመ ስልጠና መስጠት | የተሰጡ ስልጠናዎች | | 3 | | | 3 | | ዲን፣ |
| **ተግባር 8.** ለኮሌጁ የቴክኒክ ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች (ላብራቶሪ አሲስታንቶች) ስለደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትና የተመደቡበት ኃላፊነት የሚያስፈልገውን ሙያ እንዲያካብቱ ያለመ ስልጠና መስጠት | የተሰጡ ስልጠናዎች | | 1 | | 1 | | | ዲን፣ የቤተ ሙከራ ማኔጀር |
| **ተግባር 9** ከቢሮዎች፣ ከኢንዱስትሪዎች፣ ከምርምር ማዕከላት እና ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የተጠናከረ ግንኙነት በመፍጠር ተማሪዎች የተግባር ልምምድ እንዲሁም መምህራን በጋራ ምርምር እንዲሠሩ ማድረግ | የተግባር ልምምዶች ቁጥር | | 2 | | | | | ዲን |
| **ግብ 3.2. የቀጣይ አምስት ዓመታት ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት** | | | | | | | | |
| **ተግባር 1.** ዕቅድ የሚያዘጋጁ የመምህራንን ቡድን ከየትምህርት ክፍሉ በመምረጥ በአካዳሚክ ካውንስል ማጸደቅ | የቡድኖች ቁጥር | 0 | 7 | | | 7 | | ዲን |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ተግባር** 2. ስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅት መርሐ ግብር አቅርቦ ማጸደቅ | | | | | | | | ቡድኖች |
| **ተግባር** 3. ስትራቴጂክ ዕቅዱን ማዘጋጀት | የዕቅዱ ደረጃ በመቶኛ | | | | | | 75 | ቡድኖች |
| **ግብ 3.3. የሳይንስ ኮሌጅን አደረጃጀት ማጠናቀቅና የኮሌጁን ኮምፕሌክስ ለመስራት የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን መስራት** | | | | | | | | **ዲን** |
| **ተግባር** 1. አደረጃጀቱንና የኮሌጁን ኮምፕሌክስ የመነሻ ሃሳብ ለኮሌጁ መምህራንና ሰራተኞች አቅርቦ ውይይት ማድረግ | | 0 | 7 | | | 7 | | ዲንና የተቋቋመው ኮሚቴ |
| **ተግባር** 2. አደረጃጀቱንና የኮሌጁን ኮምፕሌክስ የመነሻ ሃሳብ በውይይቱ መሰረት አስተካክሎ በማቅረብ ማጸደቅ | | 0 | 7 | | | 7 | | ዲን |
| **ተግባር** 3. በጸደቀው አደረጃጀት መሰረት ተገቢ ምደባዎችን ማድረግ | | 0 | 7 | | | 7 | | ዲን |
| **ተግባር** 4. ለጸደቀውን የኮሌጅ ኮምፕሌክስ የቦታ መረጣ ማካሄድ፣ የግንባታ ፕላን ማሰራት፣ በጀት ማስመደብ፣ | | | | | | | | ዲን |
| **እይታ 4. ፋይናንስ** | | | | | | | | ዲን |
| **ተግባር** 1 ለኮሌጁ የተመደበን በጀት ለተበጀተለት ዓለማ ማዋልና በአግባቡ መጠቀም | መቶኛ | 65 | 100 | | | 75 | 100 | ዲን |
| **ተግባር** 2 አግባብ ያለውና ከብክነት የፀዳ የንብረት አጠቃቀም ስርዓት በኮሌጁ እንዲኖር ማድረግ | | | | | | | | ዲን |
| **ተግባር** 3 የተበላሹ ንብረቶችን ጥገና ማካሄድና የሚወገዱ ካሉ ማስወገድ | | | | | | | | ዲን |